# አንቀጽ 39፡ ሂሳዊ ምልከታ

**አለማየሁ ቢራራ፣ January 17, 2012**

በዚህች አጭር ጽሁፌ፣ የአንቀጽ 39ን መሰረታዊ መከራከሪያ ነጥቦች አስቀምጣለሁ። ቀጥሎም እኚህ መከራከሪያ ነጥቦች ሁለት መሰረታዊ ጉድለቶች እንዳሉባቸዉ አሳያለሁ። (1) አንደኛዉ አንቀጹ እርስ-በርሱ የሚቃረን መሆኑ ነዉ። (2) ሁለተኛዉ፣ አንቀጹ በመገንጠል አደጋነት ያስቀመጠዉ የብሄር መብቶችን መረገጥ ብቻ ነዉ። በዚህም ሌሎች የመገንጠል አደጋ ሊሆኑ የሚችሉ ምክንያቶች መኖራቸዉን (ከብሄር መብት መረገጥ በተጨማሪ) አንቀጹ ከግንዛቤ አያስገባም (ወይም ችላ ይላቸዋል)።

## 1. የአንቀጽ 39 መሰረታዊ መከራከሪያዎች

በኢትዮጵያ ህገመንግስት ዉስጥ ከተቀመጡት አንቀጾች በጣም አከራካሪ ሆኖ የተገኘ አንቀጽ ነዉ -- አንቀጽ 39። ይህ አንቀጽ ለሃገራችን ያለዉ እንደምታም ቀላል አይደለም። ሃገሪቱ እንደ አንድ ሃገር የግዛት ህልዉናዋን ጠብቃ ትቀያለች ወይስ ትበታተናለች በሚለዉ ላይ ብይን የሚሰጥ አንቀጽ ነዉ። አንቀጹ የኢትዮጵያ ብሄርና ብሄረሰቦች እስከመገንጠል መብት አላቸዉ ብሎ ይደነግጋል። አንቀጹን በሚደግፉ ወገኖችች (መንግስትን ጨምሮ) የሚንጸባረቀዉ አቋም ይህ አንቀጽ የኢትዮጵያን አንድነት ያጠናክራል የሚል ነዉ። ለዚህ ደግሞ የሚሰጠዉ መከራከሪያ እንደሚከተለዉ ነዉ፡

- አንድ ብሄር ለመገንጠል የሚፈልገዉ በባህል፣ በቋንቋዉና ክልሉን በራሱ የማስተዳደር መብቱ ላይ ጭቆና ከደረሰበት ብቻ ነዉ።
- የመገንጠል መብት መኖሩ ደግሞ ለነኚህ መብቶች ዋስትና ይሰጣል።ይህም የሚሆንበት ምክንያት ብሄር ብሄረሰቦች የመገንጠል መብታቸዉ ከተጠበቀ፣ ጭቆና በደረሰባቸዉ ግዜ የራሳቸዉን ሃገር የመፍጠር መብት ስላለቸዉ ያንን አማራጭ ይወስዳሉ። ይህ አማራጭ ካላቸዉ ደግሞ አንዱ ብሄር በሌላኛዉ ላይ ጭቆና የማድረስ አቅሙን ይገድበዋል። ይህ ገደብ ደግሞ በራሱ አንዱ ብሄር ሌላኛዉ ላይ ጭቆና እንዳይፈጽም ያደርጋል።
- ጭቆና ከሌለ ደግሞ የመገንጠል ጥያቄ አይነሳም።

አንቀጽ 39 ለኢትዮጵያ አንድነት ዋስትና ይሰጣል የሚለዉ መከራከሪያ መሰረቱ ከላይ የተጠቀሱት ሶስት ታሳቢዎች (assumptions) ናቸዉ።

እነኚህ ታሳቢዎች ሁለት ችግሮች አሉባቸዉ። አንደኛዉ የርስ-በርስ ተቃርኖ ነዉ። ሁለተኛዉ ችግር ደግሞ እኚህ መከራከሪያዎች የማያካትቱዋቸዉና የመገንጠል አደጋ ሊፈጥሩ የሚችሉ ሌሎች ሁነቶችን ከግንዛቤ አለማስገባት ነዉ። ሁለቱንም ተራ በተራ ከታች እመለከታቸዋለሁ።

## 2. የአንቀጹ የርስ-በርስ ተቃርኖ፡

ህገ-መንግስቱ የብሄር ብሄረሰቦችን መብት ዋስትና ሊሰጥ የሚችለዉ የመገንጠልን መብት ካካተተ ብቻ ነዉ የሚለዉ መከራከሪያ በዉስጡ የያዘዉ እርስ በርሱ የሚቃረን ታሳቢ አለዉ።ይህም እርስ-በርሱ ሚቃረን ታሳቢ እንደሚከተለዉ ነዉ፣ *የብሄረሰቦችን የመገንጠል መብት ህገ-መንግስቱ ማስከበር ይችላል፣ ይህዉ ህገ-መግስት ግን የብሄረሰቦችን ሌሎች መብቶች (የባህል፣የቋንቋ፣ራስን በራስ የማስተዳደር፣ወዘተ) ግን በራሱ መጠበቅ አይቻልም (በመገንጠል መብት ታግዞ ካልሆነ)።* እንግዲህ “የመገንጠል መብትን ለማስከበር ህገ መንግስቱ ለምን ዋስትና ሆነ?” ለሚለዉ ጥያቄ መልሱ “ህገ መንግስቱ ላይ ስለተደነገገ” የሚል ነዉ። በዚህ መከራከሪያ መሰረት ህገመንግስቱ ላይ የተደነገገ ነገር ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል ማለት ነዉ። “ለዚህ ተፈጻሚነቱ ዋስትናዉ ምንድነዉ?” ለሚለዉ ጥያቄ ደግሞ መልሱ “የሃገሪቱ የህግ ተቋማት ናቸዉ” የሚል ነዉ። ስለዚህ የህገመንግስቱ ዋስትና የሃገሪቱ ተቋማት ናቸዉ ወደሚለዉ ድምዳሜ ይወስደናል። የሃገሪቱ ተቋማት ለህገመንግስቱ መተግበር ዋስትና ካልሆኑ ግን የመገንጠል መብትም ሊከበር አይችልምና (የመገንጠል መብትንም አስፈጻሚ የሚሆኑት የሃገሪቱ የህግ ተቋማት ስለሆኑ)። ተቃርኖዉ የሚነሳዉ እንግዲህ እዚህ ጋ ነዉ። የሃገሪቱ የህግ ተቋማት ለህገመንግስቱ ዋስትና ከሆኑ፣ ህገመንግስቱ ዉስጥ ለሚደነገጉ ከመገንጠል ዉጪ ላሉት የብሄረሰብ መብቶች ለምንድነዉ ዋስትና መሆን

የሚሳናቸዉ? ለመገንጠል መብት መከበር የሃገሪቱ የህግ ተቋማት ዋስትና ከሰጡ፤ የብሄረሰቦች ሌሎች መብቶችን (የባህል፤የቋንቋ፤ራስን በራስ የማስተዳደር፡ወዘተ) ለመጠበቅ ዋስትና የማይሆኑበት ምክንያት ምንድነዉ? የሃገሪቱ ተቋማት ዋስትና ይሰጣሉ ካልን ደግሞ፤ የመገንጠል መብት ለምን እንደዋስትና አስፈለገ? ግልጽ የሆነ መልስ የለም።

የዚህን ታሳቢ ተቃርኖ ቀላል ምሳሌ ወስዶ ለማሳየት ያህል፤ ሁለት ብሄሮች አሉ እንበል - ብሄር “ሀ” እና ብሄር “ለ”። በህገመንግስቱ መሰረት ሁለቱም ብሄሮች አብረዉ ሲኖሩ የየራሳቸዉ መብት አላቸዉ። ይህ መብታቸዉ ህገመንግስቱ ዉስጥ ተደንግጓል። ይኸዉ ህገመንግስት፤ የትኛዉም ብሄር መገንጠል ከፈለገ መብት እንዳለዉም ይደነግጋል። ብሄር “ሀ” የብሄር “ለ”ን መብት ለመሸራረፈ ሞከረ እንበል።ለምሳሌ ብሄር “ሀ” ብሄር “ለ”ን “ቋንቋህን ለመንግስት ስራ መጠቀም አትችልም” አለዉ እንበል። እንግዲህ ብሄር “ሀ” ህገመንግስቱን ተቃርኗል ማለት ነዉ። በዚህ ግዜ የሃገሪቱ የህግ ተቋማት የብሄር “ሀ”ን ኢህገመንግስታዊ አካሄድ መግታት መቻል አለባቸዉ። አለበለዚያ ህገመንግስቱን መጠበቅ አልቻሉም ማለት ነዉ። በአንቀጽ 39 ደጋፊዎች መከራከሪያ መሰረት እንዲህ አይነቱ አደጋ ሊከሰት ይችላል (አለበለዚያ አንቀጽ 39 እንደዋስትና መቀመጡ አስፈላጊ ስላልሆነ)። በዚህም የተነሳ ብሄር “ለ” ለመገንጠል ወሰነ እንበል። ይህም ህገ መንግስታዊ መብቱ ነዉ። ነገር ግን ብሄር “ሀ”’ ብሄር “ለ”ን “ለመገንጠል አልፈቅድልህም” ቢለዉ ማነዉ የብሄር “ለ”ን የመገንጠል መብት ሚያስከብርለት? የሃገሪቱ የህግ ተቋማት ናቸዉ ሊሆኑ የሚችሉት -- በአንቀጽ 39 መሰረት። ታዲያ የህግ ተቋማቱ የብሄር “ለ”ን የመገንጠል መብት መጠበቅ ከቻሉ፤ ለምንድነዉ ከጅምሩ የብሄር “ለ” መብት ሲነካ መጠበቅ ያልቻሉት? የብሄር “ለ”ን በቋንቋ የመጠቀም መብት ማስጠበቅ ያልቻሉ የህግ ተቋማት፤ እንዴት የመገንጠል መብቱን ሊያስጠብቁ ይችላሉ? እርግጥ ነዉ፤ ተቋማቱ አስከበሩም አላስከበሩም ብሄር “ለ” በግድ ይገነጠላል ልንል እንችላለን። እንደዚያ ከሆነ ግን ሲጀመርም የመገንጠል መብት ለምን ህግ ሆኖ ተጻፈ (ተቋማቱ ሊያስፈጽሙት ካልቻሉ)? ሰለዚህ አንቀጽ 39 በአንድ በኩል የሃገሪቱ የህግ ተቋማት ለብሄሮች ህገመንግስታዊ መብቶች ዋስትና ይሰጣሉ ይላል (ካልሆነ የመገንጠል መብትም ትርጉም የለዉም)። በሌላ በኩል ደግሞ እኚሁ መብቶች ሲሸራረፉ ተቋማቱ ዋስትና ላይሰጡ ይችላሉ የሚል ታሳቢ አለዉ (ካልሆነ መገንጠል እንደዋስትና መቅረቡ አስፈላጊ አይደለም)። ይህ በአንቀጽ 39 መከራከሪያ ዉስጥ ያልተፈታ ተቃርኖ ነዉ።

## 3. አንቀጹ ታሳቢ የማያደርጋቸዉ የመገንጠል አደጋዎችና እንደምታቸዉ

አንቀጽ 39 ታሳቢ የሚያደርገዉ የመገንጠል አደጋ ከብሄር መብቶቸ ጋር ብቻ የተያያዘ ነዉ የሚል ነዉ። የመገንጠል አደጋዎች የሚመነጩት ግን ከብሄር መብቶች ጋር በተተያያዘ ብቻ አይደለም። በሌሎች ምክንያቶችም የመገንጠል አደጋዎች ሊከሰቱ ይችላሉ።ለምሳሌ በኢኮኖሚ አቅም መለያየት ጋርም ተያይዞ የመገንጠል አደጋ ሊከሰት ይችላል። ይህ አንዳንድ የአዉሮፓ ሃገሮችም ዉስጥ የተከሰተ ነገር ነዉ። ህጋቸዉ መገንጠልን ስለማይደግፍ ግን መገንጠልን አላስከተለም። በተለይ ከተፈጥሮ ሃብት መለያየት ጋር ተያይዞ የመገንጠል አደጋ ሊከሰት ይችላል። ሰዉ ሰራሽ ልዩነቶችን በተመጣጠነ እድገት ፖሊሲዎች ማስቀረት ቢቻልም፤ በተፈጥሮ ሃብት መበላለጥ ከሰዉ ቁጥጥር ዉጭ የሆነ ነገር በመሆኑ ማስቀረት ከባድ ነዉ። ይህን በምሳሌ ለማሳየት፤ አንድ በጣም አነስተኛ የህዝብ ቁጥር ያለዉ ብሄር ክልል ዉስጥ ከፍተኛ የወርቅ ወይም የነዳጅ ክምችት ተገኘ እንበል። የዚህ ክልል ህዝብ ቁጥር 3 ሚሊየን ነዉ እንበል፤ ለምሳሌ ያህል። ይህ ክልል ያገኘዉን ከፍተኛ የወርቅ ወይም የነዳጅ ክምችት ቢገነጠል ለብቻዉ መጠቀም ይችላል። ኢትዮጵያ ዉስጥ ከቆየ ግን ከሌሎች 80 ሚሊየን ህዝቦች ጋር ይካፈላል። በዚህ ሁኔታ መገንጠልን የሚደግፉ የፖለቲካ ቡድኖች በክልሉ ዉስጥ በርካታ ድጋፍ የማግኘት እድላቸዉ ጠባብ አይሆንም።እርግጥ ነዉ የኢትዮጵያ ህዝብ አብሮነቱን የሚወድ ህዝብ ነዉ።ነገር ግን፤ ከፍተኛ ሃብት እንኩዋን ብሄርን ከብሄር ጋር ይቅርና የአንድ እናት ልጆችንም ሊያጣላ ይችላል -- አጫራች ሳይሆን አስታራቂ በሆነ ስርአት ካልተዳኙ። አንቀጽ 39ም ለእንዲህ አይነቱ ክስተት ሽሚያን የሚያበረታታ እንጂ አስታራቂ አንቀጽ አይደለም።

የዚህ አይነቱ የመገንጠል ስጋት እንደምታዉ መጻኢ የመገንጠል አደጋን በመደቀን ብቻ አያበቃም። የወደፊት አንድነት ዋስትና መጥፋቱ በዛሬዉ እንቅስቃሴያችን ላይ የራሱን ተጽእኖ ያሳርፋል። ለምሳሌ በጋራ የምንጠቀምባቸዉን መሰረተ ልማቶች እንገንባ ቢባል፤ እኚህ መሰረተ ልማቶች የሁሉም ብሄር ክልል ዉስጥ መገንባት አይችሉም። አባይን መገደብ ምንችለዉ ዉስን ቦታዎች ላይ ነዉ።ቢገነባ የምንጠቀመዉ ግን ሁላችንም ነን።አየር ማረፊያዎችና ሌሎች ትልልቅ ልማቶቸም

እንዲሁ። አንድ ሃገር ደግሞ እንዲህ አይነት ለረጅም ግዜ የሚያገለግሉ ትልልቅ ኢንቨስትመንቶችን መገንባት መቻል አለበት። መተማመን ከሌለ ደግሞ ብዙ ሃብት አፍስሶ እንዲህ አይነት መሰረተ ልማቶችን አንደኛዉ ብሄር ሌላኛዉ ክልል ዉስጥ ለመገንባት ስጋት ይኖርበታል። በዚህም የተነሳ ዜጎች በጋራ መሰረተልማቶች ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ይሰጋሉ። ይህም ኢንቨስትመንትን ያቀጭጫል። የሃገርንም እድገት ይገድባል። ከዚህም በተጨማሪ ዜጎች ከራሳቸዉ ክልል ወጥተዉ ሌላዉ ክልል ዉስጥ ብዙ ኢንቨስት ማድረግ ይፈራሉ። ሃገሬ ነዉ ብለዉ ዛሬ ኢንቨስት ያረጉበት ክልል ዉስጥ ነገ የዉጭ ዜጋ ሆኖ የመገኘት ስጋት ይገድባቸዋል። እነኚህ እንቅፋቶች እንግዲህ ኢንቨስትመንት እያዳከሙ ልማትን ያቀጭጫሉ ማለት ነዉ። በርግጥ ይህ ሁኔታ አሁን ኢትዮጵያ ዉስጥ አልተከሰተም። አሁን ያለንበት የኢትዮጵያ ሁኔታ ሁሌም ይዘልቃል ማለት ግን አይቻልም። ላይሆን የሚችልበት ሁኔታ አለ። አሁን ኢትዮጵያ እየተመራች ያለችዉ ጠንካራ ማእከላዊ አመራር ባለዉ ፓርቲ ነዉ። ብዙ የተከፋፈሉ ፓርቲዎች ፓርላማ ዉስጥ ቢገቡ ሊከሰት የሚችለዉ ፍጹም የተለየ ሁኔታ ሊሆን ይችላል። ህገመንግስት ሲደነገግ ለረጅም ግዜ ታስቦ ነዉና እንዲህ የተሰበጣጠሩ ፓርቲዎችም ፓርላማዉን ቢቆጣጠሩ ሃገሪቱ ላይ ጉዳት እንዳይደረስ ዋስትና በሚሆን ሁኔታ መቀረጽ አለበት።

## 4. ማጠቃለያ

አንቀጽ 39 የመገንጠል መብትን ህገመንግስት ዉስጥ በመደንገግ የብሄር መብቶችን ዋስትና እሰጣለሁ ይላል። ይህ መከራከሪያ ግን ሁለት ችግሮች አሉት፤ አንዱ አንቀጹ ራሱ እርስ በእርሱ የሚቃረን መሆኑ ነዉ። ሁለተኛዉ ደግሞ ሌሎች የመገንጠል አደጋዎችን ከግንዛቤ ያላስገባ መሆኑ ነዉ። ተቃርኖዉ የሚመነጨዉ፤ በአንድ በኩል ህገመንግስቱ ህገመንግስት በመሆኑ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል ይላል (በህግ ተቋማት ጥበቃ አማካኝነት)። በሌላ በኩል ህገመንግስቱ ላይተገበር ይችላል ይላል (ከመገንጠል ዉጪ ያሉ የብሄር መብቶች ሊሸረሸሩ ይቸላል ይላል)። ህገመንግስቱ ህገመንግስት በመሆኑ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናለ ካልን፤ ህገ መንግስቱ ከመገንጠል ዉጪ ያሉ ሌሎች የብሄር መብቶችንም ለመጠበቅ ህገመንግስት በመሆኑ ብቻ ዋስትና መሆን አለበት። ያን ካልን ደግሞ የብሄሮች ህገመንግስታዊ መብት ሊሸረሸር ሚችልበት ሁኔታ አይኖርም። ስለዚህ የመገንጠል መብት እንደዋስትና መቀመጡ አስፈላጊ አይሆንም። ህገመንግስቱ ህገመንግስት በመሆኑ ብቻ ሊከበር የማይችል ከሆነ ደግሞ ለመገንጠል መብትም ህገመንግስቱ ዋስትና ሊሆን አይችልም።

ሁለተኛዉ የህገመንግስቱ ችግር ሌሎች የመገንጠል አደጋዎችን ከግንዛቤ ያላስገባ መሆኑ ነዉ። በተለይ የተፈጥሮ ሀብት መበላለጥ የመገንጠል አደጋን ሊፈጥር ይችላል። ይህ ስጋት ደግሞ በክልሎች መሃል መተማመንን በመቀነስ ኢንቨስትመንትን ያዳክማል። የሃገር እድገትንም ሊገድብ ይችላል።